# የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) ፕሮግራም

**(በብልጽግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ)**

**መጋቢት 2014 ዓ.ም**

**ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና)**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

ገፅ


መግቢያ...........................................................................5

ክፍል አንድ .....................................................................8

I. የብልጽግና ፓርቲ ዓላማና መለያ ዕሴቶች ..................8

1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል ዓላማ፦ “የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ”........................................9

1.2 መለያ ዕሴቶቻችን..........................................................9

1.2.1 ኅብረ ብሔራዊ አንድነት...............................10

1.2.2 .የዜጎች ክብር..................................................11

1.2.3 ነጻነት...............................................................12

ክፍል ሁለት........................................................................13

II. የፖለቲካ ፕሮግራም.........................................................13

2.1 የፖለቲካ ፕሮግራም ዓላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ መንግሥት መገንባት፣.....................13

2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች............................................13

2.2.1 ጠንካራና ቅቡል ሀገረ መንግሥት በጽኑ መሠረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሀገራዊ መግባባት መፍጠር.........................................13

2.2.2 በተቋማዊና ሕዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት........................15

2.2.3 ዘላቂና አዎንታዊ ሰላምን ማረጋገጥ..................19

ክፍል ሶስት......................................................................... 21

III. የኢኮኖሚ ፕሮግራም ........................................................21

3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ዓላማ:- ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት……………..............................21

3.2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች........................................21
3.2.1 የብዝኃ ዘርፍ የኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት..........21
3.2.2 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረገ ማኅበራዊ ፍትሕ ማረጋገጥ..........25
3.2.3 ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት................................................27
3.2.4 ከተሜነት እና የከተማ ልማትን ማስፋፋት............28

ክፍል አራት ..............................................................30
IV. ማኅበራዊ ፕሮግራም......................................................30
4.1 የማኅበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፡-ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማኅበራዊልማት…...............................................30
4.2 የማኅበራዊ ፕሮግራም ግቦች..........................................30
4.2.1 ፍትሐዊነት፣ ጥራት እና አግባብነት ያለው የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማረጋገጥ...................30
4.2.2 መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና ሥርዓት መዘርጋት................................................ 32
4.2.3 የሀገራችንን ዐቅም ያገናዘበ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓት መዘርጋት.......................................33
4.2.4 የሴቶችንና ወጣቶች የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት........................... 34
4.2.5 ብዝኃነታችንን ማዕከል ያደረግ የቋንቋ የባህልና ቅርስ ልማት.................................................... 35

ክፍል አምስት.......................................................... 37
V. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም ..........................................37
5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና ዓላማ፡- ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት....................................37

5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች ..........................................37
5.2.1 ሀገራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት.....37
5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት.........................38
5.2.3 የብዙዮሽ ትብብር ተቋማት ተሰሚነትን መጨመር እና ፖሊሲያዊ ነጻነትን ማስከበር.........39
5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ......................39
5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ ማሳደግ..............................................40
5.2.6 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት የመፈፀም አቅም መገንባት..............................................41

# መግቢያ

I. ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን አስመዝግባለች። እነዚህን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች አስጠብቆ ለማስፋት፣ ስሕተቶችን ለማረም እንዲሁም የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት በዘላቂነት ለማሟላትና ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር የኢሕአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ወቅቱ ለሚጠይቀው ትግል በሚመጥን መልኩ ለመደራጀት አምነው የፈጸሙትን ውሕደት መነሻ በማድረግ ይህ የ"ብልጽግና ፓርቲ" ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

II. በሀገራችን ተጠብቀው መስፋት ያለባቸው በርካታ ድሎች ተመዝግቧል። በኢኮኖሚው መስክ ሀገራችን ለተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችውን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ የድህነት ቅነሳ፣ የመሠረተ ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎት መስፋፋት ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። በፖለቲካው መስክ የተዘረጋው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ሕገ መንግሥታዊ ፌደራላዊ ሥርዓት ጉድለቶቹን አርሞ መሄድን ይጠይቃል። በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረክ የፍትሕና የገለልተኝነት ተምሳሌት መሆኗን አስጠብቀን መዝለቅ ይጠበቅብናል።

III. በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት የታዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስሕተቶችን ያለማወላወል ማረም ያስፈልጋል። አሁን ሀገራችን በደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ከዚህ በፊት በተከተልነው የልማት ፋይናንስ ሞዴል በኢኮኖሚና የማኅበራዊ መስክ ያስመዘገብነውን ዕድገትና ልማት በተመሳሳይ መንገድ አስጠብቆ ማስቀጠል ከባድ ፈተና የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ያስመዘገብነውን የኢኮኖሚ ዕድገቱን አንድም የዕድገት ምንጮችን በማስፋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግሥት ጉድለት ምክንያት የተፈጠረውን የሀገር ሀብት ብክነትና ዝርፊያ በመከላከል፣ የሀገራችንን ሕዝቦች ፍትሐዊና የላቀ ተጠቃሚነት

ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመሆኑም ምርታማነትን የሚያሳድግና በግሉ ባለሀብትና በመንግሥት ትብብር የሚገነባ የኢኮኖሚ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። የግሉ ባለሀብት በሀገራችን ውስጥ በቂ ሀብት የሚፈጥርበትንና ምርታማነት የሚያድግበትን የፋይናንስ ሞዴል መከተል ይጠይቃል።

በፖለቲካው መስክ የብሔር ማንነትን እና ሀገራዊ ማንነትን፤ አጣጥሞ በዘላቂነት የሚያስኬድ የሀገርና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል። ህብረተሰብን በጎራ በመክፈል አግላይ የነበረው አካሄድና አደረጃጀት አቃፊና አካታች ሆኖ የሀገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ ችግር በሚፈታ ማእቀፍ ሊሻሻል ይገባል። የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕንቅፋት የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ከዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የላቁ ናቸው የሚለው ምሉዕነት የጎደለው ትንተናና የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግናን በሚያስቀድሙ የፖለቲካ ዕይታዎች መተካት ይኖርበታል። የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲያችን መቀጨጭ ታርሞ ግልፅና ለሁሉም የሀገራችን ህዝቦች የዴሞክራሲ ሥርዓት ማሳያ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

IV. ሀገራችን ኢትዮጵያን የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር አስተማማኝ መሰረት ዛሬ ላይ በመገንባት ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ የዜጎች ክብር፣ ፍትሕ እና የጋራ ብልጽግና የተረጋገጠባት ሀገር መሆን ይኖርባታል። ኢሕአዴግ በትጥቅ ትግል ለድል ከበቃ በኋላ ለ28 ዓመታት ሀገርን በመራበት ታሪኩ የተንቀሳቀሰበት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አውድ ተለውጧል። በተያያዘም ኢሕአዴግና አጋር ድርጅቶች ሲከተላቸው የነበሩ የርእዮተ ዓለም ዕሳቤዎች ፖለቲካዊ አዋጭነታቸው መንምኗል። ፓርቲያችን ከዘመናዊ የፖለቲካ ጨዋታ ሕግጋት ጋር ተናቦ የሚሄድ የዕይታ ለውጥ በአጭር ጊዜ በማካሄድ እየተለወጠ ካለው ምኅዳር ጋር መዋጀት እና እንደ ሀገርም ከፍተኛ ጥፋትን ሊያስከትል ከሚችል የቆሞ ቀርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት ወሳኝ ነው።

V. በጥቅሉ ሀገራችን በኢሕአዴግ አመራር በቆየችባቸው ዓመታት የነበሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ጠብቆ ማስፋት፣ ጉድለቶችን ነቅሶ በማውጣት ያለማወላወል እንዲታረሙ ማድረግ እና የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት ማሟላት ያስፈልጋል። ሆኖም ግን በቀድሞ ኢሕአዴግና አጋር ድርጅቶች ቅርጽና ይዘት እነዚህን ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ ስሕተቶችን ማረም እና የመጭውን ትውልድ ጥቅም የማስከበር ዓላማዎችን በተሟላ መልኩ ማሳካት አይቻልም። በመሆኑም የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን እና አጋር በሚል ሲጠሩ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማካተት፣ አቃፊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚገነባ "የብልጽግና ፓርቲ" የሚሰኝ ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲ ማቋቋም አስፈልጓል።

VI. ወጥ ዓላማ ያለው ኅብረ ብሔራዊ ውሑድ ፓርቲ መሆን ሰፊውን የሀገራችንን የሕዝብ ክፍል የሚያቅፉ ነገር ግን በዕይታ ግድፈት ከሀገራዊ የፖለቲካ ውሳኔ የተገለሉትን ኢትዮጵያዊያን በእኩልነት የሚሳተፉበትን ፓርቲያዊ አወቃቀር ለማምጣት ያስችላል። በሌላ በኩል ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲው አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ብሔሮች በሚያሳትፍ እና በሚያካትት መልኩ ውክልና እና ብቃትን መሠረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ትሥሥሮሽን በማጠናከር በሐሳብ ልዕልና ላይ የተመሠረተ ዘመናዊ የፖለቲካ ፉክክርና ትብብር መሠረት እንዲይዝ በማድረግ ሀገራችን የተያያዘችው ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ኖሮት ከማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ እና እንዲጠናከር የሚያግዝ ይሆናል።በአጠቃላይ እውነተኛ ኅብረ ብሔራዊ የሆነው ውሑድ ፓርቲያችን የዓላማና የተግባር ውህደት በማምጣትና የተሻለ ኃይል በማሰባሰብ በቀጣይ ለላቀ የዓላማ አንድነትና ሀገራዊ ድል የሚያበቃ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አቅጣጫ የሚከተል ይሆናል።

# ክፍል አንድ

## 1. የብልጽግና ፓርቲ ዓላማና መለያ ዕሴቶች

ፓርቲያችን ሀገራችንን የሚመለከትበት የዕይታ ማሕቀፍ በጥቅሉ የነበረውን ጠንካራ መሠረት በማስጠበቅ እና ውሱንነቶችን በማረም ሁለንተናዊ የብልጽግና ምእራፍ መክፈት የሚል ነው። ይህን የዕይታ ማዕቀፍ በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በተለያዩ ቡድኖች፣ መደቦች፣ ማንነቶች፣ ወዘተ የሚስተዋሉ ዋልታ-ረገጥ አስተሳሰቦች ሚዛን ጠብቀው እንዲሄዱ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ከወግ አጥባቂ ዝንባሌዎችም ሆነ አፍርሰው ከሚገነቡ አስተሳሰቦች ይልቅ የሀገራችንን ተጨባጭ ችግሮች የሚፈታ፣ ህዝቡን የሚጠቅም፣ በመግባባትና በውጤት ላይ የሚያተኩር እንዲሁም ከርዕዮተ ዓለም ጥገኝነትና እስረኝነት የተላቀቀ የመካከለኛው መንገድን ተመራጭ ያደርጋል።

በሀገራችን የቀኝ እና የግራ አሰላለፍ ልማድ በመሠረቱ ከመደባዊ ውግንናና ዝንባሌ ይልቅ አጠቃላይ በሀገረ መንግሥቱ ዙሪያ ባሉ ዕይታዎች ላይ የሚያጠነጥን መሆኑን በመረዳት እነዚህን አመለካከቶች የሚያቀራርብ አሰላለፍን ይከተላል። ይህ አተያይ ሁኔታዎችን ቋሚ አድርጎ ከመመልከት ይልቅ ነባራዊ እውነታን እያነበበ፣ ቋሚ መርሆችን ማዕከል አድርጎ ጉዞን የመፈተሽ እና በጥናት ላይ እየተመሰረተ የሚቀጥል መርሕ ተኮር የተግባራዊነት ዕሳቤን ይከተላል። በዚህም ምክንያት ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያሰባስብና የፓርቲው የማኀበራዊ መሠረት ማድረግ የሚያስችል አካታች ፖለቲካዊ ጉዞን ተመራጭ ያደርጋል። ፓርቲያችን "ሀገራችን ለሁላችንም ትበቃለች" የሚል ጽኑ ሐሳብ በመያዝና የእጦት አስተሳሰብን በመሻገር ለሁሉም ዜጎች የምትሆንና ሁሉም በኩራትና በምቾት የሚኖርባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ትግል ያደርጋል። ይህንን ዓላማ የሚፃረሩ በግራም ሆኑ በቀኝ የተሰለፉ አፍራሽ አስተሳሰቦችንና ተግባሮችን ሁሉ ፓርቲያችን በጽኑ ይታገላል።

## 1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል ዓላማ፦ “የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ”

የፓርቲያችን ጥቅል ዓላማ የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው። ብልጽግና ስንል ፈርጀ ብዙ ትርጓሜን አዝሎ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና የማኀበራዊ ገፅታ ያለው ነው። የኢኮኖሚ ብልጽግና፣ የሕዝቦች መሠረታዊ ፍላጎቶች በተገቢና በዘላቂነት ለማሟላት ፈጣን እና ሁለንተናዊ ዕድገትን በማስመዝገብና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ያለው ኢኮኖሚ በመገንባት ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና የህዝቦችን ድኅነትና ኋላ ቀርነትን ለመቅረፍ መቻልን ያካተተ ነው። የፖለቲካ ብልጽግና ስንል ለዴሞክራሲ ባህል ማበብ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በመገንባት፣ የሕዝቦች ነጻነትና እኩልነት ተረጋግጦ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረውላቸው የሚኖሩባት፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ፣ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ጽኑ መሠረት ላይ ማቆም ማለታችን ነው። የማኀበራዊ ብልጽግና መልካም ሀገራዊ ወጎችን፣ ዕሴቶችን እና ባህሎችን በማዳበር በሥነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ማፍራት፣ በአካልና በአእምሮው የዳበረ ጤናማ ዜጋ መፍጠር፣ ከአስከፊ የማኀበራዊ ችግር የተጠበቀ ኅብረተሰብ መገንባት እና በሕዝቦች መካከል አዎንታዊ ሰላም በመፍጠር ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ ማለት ነው።

## 1.2 መለያ ዕሴቶቻችን

ዕሴቶቻችን ቅድሚያ ዋጋ የምንሰጣቸውና የምንታገልላቸው ወደ ብልጽግና ዓላማ የመድረሻ መንገዳችን አመልካቾች ናቸው። በምንጓዝበት መንገድ ሁሉ በሚገጥሙን የተለያዩ አጣብቂኞች ቅድሚያ የምንሰጠው የዜጎችና የሕዝቦች ክብር፣ ነፃነት፣ ፍትሕ፣ ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት፣ መከባበርና መቻቻል፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ አሳታፊነት ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ይሆናሉ። ለአብነትም መለያ እሴቶቻችን እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

### 1.2.1 ኅብረ -ብሔራዊ አንድነት

የፓርቲያችን ዋነኛ ዓላማ ኅብረ ብሔራዊነቱ የተጠበቀ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መገንባት ነው። ኅብረ ብሔራዊ ስንል የብሔር፣ የሃይማኖት ወይም ሌላ ማንነቶችን ያቀፈና ማንንም ያላገለለ ማኅበረሰብ ማለታችን ነው። የፓርቲያችን ኅብረ ብሔራዊነት በሁሉን አቀፍነት፣ በብዝኃ ልሳንነት እና በአሳታፊነት ሊገለጽ ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ብዝኃነትን እንደጸጋ የሚመለከት ለሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዕውቅና የሚሰጥና ካላቸው የታሪክ ትሥሥር፣ ተመሳሳይ አሁናዊ ሁኔታ፣ የጋራ ጥቅም እና ተስፋ በመነሣት ጠንካራ ኅብረትና ትብብር ሊኖራቸው ይገባል የሚል ዕሴት ነው።

ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ማንነታችን እርስ በርሱ የተጋመደ፣ የተሠናሰለ እና የተዋሐደ መሆኑን አመላካች ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ዕጣ ፈንታችን እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ ለጋራ ዓላማና ግብ አብረን መቆም፣ አብረን መሥራት፣ መደጋገፍ እና መተጋገዝ እንደሚገባን የሚያስገነዝብ አመለካከት ነው። ኅብረ ብሔራዊ፣ አንድነት ታሪካዊና ነባራዊ በደሎች ከማድበስበስ ይልቅ ታርመው እንዲሄዱ፣ ይህም ለቁርሾ ሳይሆን ወዳጅነትን ለማጠናከር እንዲውል የሚያደርግ አካሄድ ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ የሚከፋፍሉ እና የሚያጣሉ ትርክቶችን ከማጉላት ይልቅ የሚያቀራርቡና የሚያስተሣሥሩንን እውነታዎች በማጉላት፣ ከትናንት ጠቃሚ ትምህርቶችን በመውሰድ እንዲሁም ዛሬና ነገ ላይ በማተኮር እኅታዊ/ወንድማዊ ኅብረትን በብሔሮች መካከል ማጠናከርን ይመርጣል። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ብዙ ሆነን አንድ፣ አንድ ሆነንም ብዙ የምንሆንበት፣ ለጋራ ግብና ዓላማ የምንደመርበት ቀመር ነው። በብዝኃነታችን ደምቀን፣ በአንድነታችን በርትተን ወደፊት የምንራመድበት የውበትና የጥንካሬያችን ምንጭ ነው።

ፍትሕ ከሰፈነ፣ ሰብአዊ ክብር ከጎለበተ እና ብልጽግና ከመጣ እንደ ሀገር የመቀጠል ተስፋችን ይለመልማል። ሆኖም ግን ኅብረ ብሔራዊ አብሮነት እነዚህ ምሦሶዎች ከተሳኩ በኋላ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን ለዓላማዎች ስኬትም ዓይነተኛ ድርሻ የሚወጣ አስቻይ አቅም በመሆኑ

ፓርቲያችን "በኅብረት ሆነን እንበለጽጋለን፤ በልጽገንም በኅብረት እንኖራለን" በሚል መርሕ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ትኩረት ይሠራል።

### 1.2.2. የዜጎች ክብር

የዜጎች ክብር ስንል ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ልታስጠብቅላቸው የሚገቡ በዜግነታቸው ሊያገኙ የሚገባቸውን ክብር እና በሀገራቸው ለመመካት የሚያስችላቸውን ሁኔታ ማለታችን ነው። የብልጽግና ፓርቲ ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሊከበር ይገባል ብሎ ያምናል። ዜጋ ሃይማኖቱ፣ ብሔሩ ወይም ጾታው ብሎም ሀብቱና ድህነቱ ከግምት ሳይገባ መሠረታዊ ፍላጎቱ ሊከበርለት፣ በእኩል ዓይን ሊታይ እና ፍትሕን ሊያገኝ ይገባል ብለን እናምናለን። በመሆኑም የዜጎች ክብር ስንል በሀገራችን ማንኛውም ቡድን ወይም ግለሰብ ከሌሎች የተለየ ተጠቃሚ አሊያ ተጎጂ እንዳይሆን መሥራት ማለታችን ነው። የዜጎች ክብር ስንል ኢትዮጵያውያንን በእኩል ዓይን የሚያይና የሚዳኝ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሕግ ፊትና በሀገራችን በእኩል የሚታዩበትና በፍትሐዊ መልኩ ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ የብዙኃንም ሆነ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔሮች መብትና ነጻነት የሚከበርበት፣ ሰው በሰውነቱ በእኩል የሚታይበት፣ ከበደልና ጭቆና ነጻ የሚሆንበት፣ በዋና ዋና የሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ዜጋ በውሳኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት እንዲሁም የሀብት፣ የሥልጣንና የመብት ክፍፍሉ ርዕታዊና አግባብ፣ ለኅሊና የማይቆረቁር የሆነበት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት መፍጠር ማለታችን ነው።

የዜጎች ክብር፣ የግለሰብና የቡድኖች እኩልነት እና የሀገር ሉዓላዊነትን አቅፎ በግለሰብ፣ በማኅበረሰብ እና በሀገር ደረጃ የሚታይ ነው። ማኅበረሰባዊና ሀገራዊ ክብር ሕዝቦች በሀገራቸውም ሆነ በዓለም መድረክ ቀና ብለው ለመሄድ መቻል ነው። ይህ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው። በዋነኝነት በሀገር ውስጥ የፍትሕና የብልጽግና ጥያቄዎችን በመመለስ እንዲሁም ከሀገር ውጭ የኢትዮጵያውያንን ደኅንነትና መብት በማስከበር ኢትዮጵያውያን በሀገራቸውና በማኅበረሰባቸው

ክብር እንዲሰማቸው ማድረግ ማለት ነው። በተመሳሳይም ደግሞ በዓለም መድረክ ስሟ በበጎ የሚነሣ ሀገር በመገንባት የሕዝባችንን ክብር ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በዜግነት ክብር የሀገራችንን ስም ከፍ ማድረግ፤ ከፍ ያለች ሀገር በመገንባት ደግሞ የዜግነት ክብርን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተመጋጋቢነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው።

በመሆኑም ፓርቲያችን በሀገራችን የሕግ የበላይነትን በማስፈን፣ ሐቀኛ የፍትሕ ሥርዓት በመገንባት፣ መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን በማክበር፣ የማኅበራዊ ፍትሕን በማረጋገጥ፣ የማኅበረሰባችንን ሰላምና ደኅንነት በመጠበቅ፣ ሰዎችን የሚያስቀድም የኢኮኖሚ ዕድገትን በማሳለጥና ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን በማምጣት ሰብአዊ፣ ማኅበረሰባዊ እና ሀገራዊ ክብርን ለማስጠበቅ ይታገላል።

## 1.2.3 ነጻነት

ከፓርቲያችን ዕሴቶች አንዱ ዜጎች የራሳቸውን የሕይወት ርዕይ የመምረጥና በመረጡት መንገድም የመኖር መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ ነው። የማኅበራዊ ዕሴቶችንና ጥቅሞችን ማስጠበቅ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሰው ሀሳቡን በነፃነት እንዲገልጽ፣ የፈለገውን እምነት እንዲከተል፣ ከፈለገው ጋር እንዲሰባሰብና እንዲደራጅ ነፃነት ካላገኘ ብቁና መልካም ኅብረተሰብ ሊፈጠር አይችልም ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። በግድና በጉልበት እነዚህ ነጻነቶቹ ተገድበውበት የሚኖር ኅብረተሰብ ምንም እንኳን ቁሳዊ ፍላጎቶቹ ቢሟሉም ቁሳዊ ያልሆነው ማንነቱ ግን ችግር ውስጥ እንዳለ መረዳት አስፈላጊ ነው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ነጻነትን ማረጋገጥ ያልቻለ ሥርዓት በአንድ በኩል ዜጎችን ንቁና ምርታማ እንዳይሆኑ የሚያደርግ፣ ሀብት ፈጠራን የሚገድል እና በጥቅሉም የብልጽግና ጉዞን የሚኮደኩድ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ሲፈጥር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቁርሾና ብሶትን የሚያቀጣጥል፣ የሐሳብ ልውውጥን የሚያሳሳ እና ፍርሃትን የሚያነግሥ የፖለቲካ ድባብን ይፈጥራል። በመሆኑም ፓርቲያችን የሀገራችንን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታትና የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ይቻል ዘንድ ነጻነትን አንዱ ዕሴቱ አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

# ክፍል ሁለት

## II. የፖለቲካ ፕሮግራም

### 2.1 የፖለቲካ ፕሮግራም ዓላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ መንግሥት መገንባት፣

የብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ዋነኛ ዓላማ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው፣ የብሔር ማንነትን እና የሀገራዊ አንድነትን ሚዛን የጠበቀ ሀገረ መንግሥት መገንባት ነው። ከጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ አንጻር ፓርቲያችን ሕዝብ ከቀጥተኛ የህልውና አደጋ ተጠብቆ የልማት፣ የእኩልነት እና የነጻነት ፍላጎቶቹ እንዲሟላለት የሚያስችል ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃትን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ተቋማዊ አደረጃጀት መገንባት ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የሀገረ መንግሥት ግንባታ ጅምራችን ጠንካራና የማይናወጥ ተቋማዊ መሰረት ያለው እንዲሆን የብልጽግና ፓርቲ ግቡ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። የብልጽግና ፓርቲ ዴሞክራሲን በተቋማዊና ሕዝባዊ ባህል ላይ መገንባት አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል። በሌላ በኩል ከሀገረ መንግሥት ቅቡልነት አንጻር የብልጽግና ፓርቲ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ጥንካሬን ለማሳደግ በሕገ መንግሥታችን የተቀመጠውን አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመፍጠር ግብ ለማሳካት ይሠራል። በመሆኑም የሀገረ መንግሥቱን ቅቡልነት በሚጨምሩና ሀገራዊ መግባባትን በሚያመጡ፣ የሕዝቦችን ግንኙነት በሚያሳልጡ እና የእውነተኛ ዕርቅ መንፈስን በሚያጎለብቱ ፖለቲካዊ ርምጃዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ፓርቲያችን የሀገረ መንግሥት ግንባታችን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የተላበሰና ብዝኃነትን የሚያንፀባርቅ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል።

### 2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች

#### 2.2.1 ጠንካራና ቅቡል ሀገረ መንግሥት በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት የሚያስችል ሀገራዊ መግባባት መፍጠር

2.2.1.1 የብልጽግና ፓርቲ የቆመላቸው የፖለቲካ ዓላማዎች

እንዲሳኩ ፓርቲው ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው ነገሮች አንዱ የሀገራዊ መግባባት ጉዳይ ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓቱ ምቹ መደላድል እንዲኖር ለማድረግ፣ የሀገረ መንግሥቱን ቅቡልነትም ከፍ ለማድረግ የብልጽግና ፓርቲ ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር በጽኑ ይሠራል።

2.2.1.2 የብልጽግና ፓርቲ በሀገሪቱ ልሂቃን መካከል የሚታየው ዋልታ ረገጥነት እና እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ሳይቀር ያለው ቅራኔና አለመተማመን ጤናማ እንዳልሆነ ይገነዘባል። ፓርቲው የሐሳብ ልዩነቶች እንዲሁም የጥቅምና የፍላጎት አለመጣጣሞች ተፈጥሯዊ መሆናቸውን ይረዳል። እንደዚህ ያሉ ልዩነቶች አይቀሬና በዴሞክራሲ አግባብ ሊስተናገዱ ቢችሉ ጠቃሚና ገንቢ ናቸው ብሎም ያምናል። ነገር ግን ሀገራዊ ህልውናን እና ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጠያያቂ የሚያደርጉ፣ የሀገረ መንግሥቱን ቅቡልነት የሚሸረሽሩ የከረሩ አለመግባባቶች ግን አሉታዊ ተጽዕኖቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም የብልጽግና ፓርቲ እጅግ መሠረታዊ በሆኑና ለሀገረ መንግሥቱ ቅቡልነት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ጠንካራ ሀገራዊ መግባባት እንዲዳብር ይሠራል።

2.2.1.3 ፓርቲያችን ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሠራቸው ተግባራት አንዱ በሀገራችን የቂምና የጥላቻ ታሪክ ምዕራፍ እንዲዘጋ ማድረግ ነው። ይህን ለማሳካት ባህላዊና ዘመናዊ የዕርቀ ሰላም ግንባታ አማራጮችን በመጠቀም ዕርቀ ሰላምን ለማምጣት በቁርጠኝነት ይታገላል። ለቀጣዩ ትውልድ ቂምና ቁርሾ ሳይሆን ሰላም፣ ወንድማማችነትንና እኅትማማችነትን ለማውረስ የዕርቀ ሰላም አማራጮችን ሁሉ አሟጦ ይጠቀማል።

2.2.1.4 የሐሳብ ልዩነቶችን ለማጥበብ እና ቅራኔዎችን ለማስወገድ ፓርቲያችን በጥናት ላይ የተመሠረተ ውይይቶችን እና ሕዝባዊ ተዋሥዖዎችን የሚያስቀድሙ ድርድሮችን በተከታታይና በቀጣይነት እንዲካሄዱ በማድረግ ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር ይሠራል። በነጠላ ጉዳዮች ላይ የጠለቁ ውይይቶች እንዲካሄዱ በማድረግ ቅራኔዎችን ደረጃ በደረጃ እየፈቱ ለመሄድ በትጋት ይንቀሳቀሳል።

2.2.1.5 የብልጽግና ፓርቲ በሀገራችን የምንፈጥረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የጠበቀና የሁሉም ማንነቶች ነፀብራቅ የሆነ፤ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ባህልና ማንነት የጠበቀ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ስለሆነም የምንገነባው ማኅበረሰብ ኅብረ ብሔራዊና በአጠቃላይም ኅብረ ማንነታዊ እንዲሆን፣ ዜጎችም ብዝኃነትን የተረዱና የሚያከብሩ እንዲሆኑ አበክሮ ይሠራል።

## 2.2.2 በተቋማዊና ሕዝባዊ ባህል ላይ የቆመ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት

2.2.2.1 የብልጽግና ፓርቲ የበለጸገችና ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ያለ ዴሞክራሲ እውን ማድረግ አይቻልም ብሎ ያምናል። የሕዝቦች ድምር የልማት፣ የእኩልነት እና የነጻነት ፍላጎት የሚያሟላ ሁለገብ የሆነ ብልጽግና እንዲመጣ የዴሞክራሲ አጀንዳ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ፓርቲያችን የሕዝብ ሉዓላዊነት መከበር እንዳለበትና የመንግሥት ሥልጣን በሕዝብ ይሁንታና ውክልና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ሊገኝ እንደሚገባ ያምናል። ዴሞክራሲ የሕዝብ ወኪሎች ከሚመረጡበት የምርጫ ሂደት አልፎ በይዘቱም የሕዝቦች እኩልነት፣ ነጻነት እና ውክልና የሚረጋገጥበት እንዲሆን ይታገላል። የብልጽግና ፓርቲ ዴሞክራሲ በትምህርት፣ በጤና፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ በመታጀብ አሰላሳይ፣ ሞጋችና

ፈጣሪ ኅብረተሰብ በመገንባት ረገድ አስተዋጽዖ ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የምንገነባው ዴሞክራሲ ተቋማዊ መሠረቱ ጽኑ እንዲሆንና ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶች የዳበሩ እንዲሆኑ ብሎም ወደ ባህልነት ደረጃ እንዲያድጉ ፓርቲያችን ይሠራል። በሀገራችን አስተማማኝና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመሥርቷል ልንል የምንችለው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአስተማማኝና በጠንካራ ተቋማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ባህል መሠረት ላይ ሲታነጽ እና ሥርዓቱ ራሱን እያጠነከረ መደበኛ ሂደት ውስጥ በመግባት የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ይህ የማይቀለበስ የዴሞክራሲ ጉዞ ብዙ ዓመታትን ሊፈጅ የሚችልና በመሰናክሎችም የታጀበ ውጣ ውረድ ያለው መሆኑን በመገንዘብ ፓርቲያችን ጽኑ ትግል ያደርጋል።

2.2.2.2 የምንገነባው የዴሞክራሲ ሥርዓት የግለሰብ መብቶችንና የቡድን መብቶችን ሳያበላልጥ የሚያስከብርና ሁለቱንም የመብት ዓይነቶች ለማስከበር በየባህሪያቸው ልክ የተቀየሰ አቅጣጫን ይከተላል። ፓርቲያችን የግለሰብና የቡድን መብት ተነጣጥለው ሊሄዱ እንደማይችሉ ይገነዘባል። የግለሰብ መብትን በተሟላ መልክ ለማክበር ለቡድን መብቶችም እኩል ዕውቅና እና ትኩረት መስጠት እንደሚገባ፣ እንዲሁም የቡድን መብቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲከበሩ ለማድረግ የግለሰብ መብቶችን ማክበር አስፈላጊ እንደሆነ ፓርቲያችን ያምናል። ይህን እውን ለማድረግም ፓርቲያችን እውነተኛ፣ ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሥርዓት ለማጠናከር በጽኑ ይታገላል። ፓርቲያችን የፌደራል ሥርዓቱ ዋና ምሦሶ ብዝኃነትን ለማስተናገድ እና ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ማጠናከር መቻሉ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዕውቅና የሰጠ ፌዴራላዊ ሥርዓት በመገንባት ኢትዮጵያ የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች

መብት የተከበረባት እውነተኛ ኅብረ ብሔራዊት ሀገር እንድትሆን ይሠራል። በአንጻሩም የግለሰብ መብቶችን በተመሳሳይ በሕገ መንግሥት ማሕቀፍ ሥር ማስከበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

2.2.2.3 እንደ ኢትዮጵያ ብዝኃነት በሚንፀባረቅባቸው ሀገራት በፉክክር ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን የትብብር እና የፉክክር ሚዛንን የጠበቀ የዴሞክራሲ ሥርዓት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። ስለዚህ ፓርቲያችን ለትብብርና መግባባት ትኩረት የሚሰጥ የሥልጣን ክፍፍልና ውክልና፣ እራስን በራስ የማስተዳደር ያልተማከለ ፌደራላዊ ሥርዓት እና ታላቅ ቅንጅትን መሠረት ያደረገ የጋራ አስተዳደር እንዲሁም ትንሽ ቁጥር ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች መብት በልዩ ሁኔታ የሚያስከብር፤ አካታችና የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ በማድረግ፤ በሂደት በሐሳብ ልዕልና ላይ የተመሠረትተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ይታገላል።

2.2.2.4 ብልጽግናን ማረጋገጥ እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውጥን ያለ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ሞያዊ ብቃት ያዳበሩ ተቋማት እውን ሊሆን እንደማይችል ፓርቲያችን በጽኑ ያምናል። ስለሆነም የዴሞክራሲ ግንባታ ሥራዎቻችን ለተቋማት ግንባታና አሠራር ቅድሚያ የሚሰጡና በዚያ ዙሪያ የሚያተኩሩ ይሆናሉ። ስለዚህም ፓርቲያችን የሕዝብ አስተዳደር፣ የዴሞክራሲ፣ የሰላም እና የደኅንነት እንዲሁም የሕግ አስከባሪና የፍትሕ ተቋማት እንደየ ባህሪያቸው ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ በትጋት ይሠራል። የመንግስትና የፓርቲ አሠራሮች በሀገራችን የመደበላለቅ መሠረታዊ ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ ፓርቲያችን ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል።

2.2.2.5 ፓርቲያችን የጸጥታና የደኅንነት ተቋማት በዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ የታነፁ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ለሀገር እና

ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ፤ ወገንተኝነታቸው ለሀገር ብቻ የሆኑ ተቋማት ለመፍጠር ይታገላል። በዚህም ረገድ በየተቋማቱ ያለውን የሞያ ብቃት እና ክሂሎት፣ እንዲሁም አደረጃጀት ከአካባቢው ሁኔታ እና ከዘመናችን የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር አቆራኝቶ ተቋማቱን ለማጠናከር በትኩረት ይሠራል።

2.2.2.6 የሀገረ መንግሥቱን ጥንካሬ ለማጎልበት እንዲሁም ተቋማት የተጣለባቸውን ሕዝባዊ አደራ እና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ሀገረ መንግሥቱ የተዋቀረባቸው ተቋማት ባህሪ እና ተልዕኮን ማዕከል ያደረገ፣ በዕውቀት የሚመራ፣ የየዘርፉን ልዩ ባህሪ ያገናዘበ፣ ለአመራር ብቃት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ያልተማከለ የተቋማት ሪፎርም እንቅስቃሴ ፓርቲያችን ተግባራዊ ያደርጋል።

2.2.2.7 ፓርቲያችን ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ፣ ሕጋዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሁሉ ሕገ መንግሥትን የተከተሉ መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል። የሕግ አውጭው፣ የሕግ አስፈጻሚው እና የሕግ ተርጓሚው የሥልጣን ክፍፍል በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆንና የእርስ በርስ ቁጥጥርና ሚዛን እንዲጠናከር፣ የመንግሥት አካላት ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ፣ ሕግ አውጭውን የሚያጠናክሩና የዳኝነት አስተዳደሩን የሚያጎለብቱ አሠራሮች እንዲዘረጉ ያደርጋል። ፓርቲያችን ሕገ መንግሥቱ መሻሻል ያለበት ሕዝብን ባሳተፈ እና ሕገ መንግሥቱ ራሱ ባስቀመጠው መንገድ ሕግና ሥርዓት በተከተለ አካሄድ ብቻ መሆን አለበት ብሎ ያምናል።

2.2.2.8 ፓርቲያችን በፌዴራል ሥርዓቱ በማንኛውም ጊዜ የሚነሡ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች ሕጋዊ፣ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ እንዲሁም የሕዝቦችን አብሮነት፣ ወንድማማችነትና እኅትማማችነት በሚያጠናክር መልኩ እንዲፈቱ ይታገላል።

2.2.2.9 የብልጽግና ፓርቲ በዚህ ፕሮግራም የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የመንግሥት ተቋማትን የማስፈጸም ዐቅም ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። የፓርቲውን ፕሮግራም ለማሳካት ዕንቅፋት የሚሆኑ፣ የሀገር እና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዱ ከኅሊና ቢስነት የሚመነጩ ብልሹ አሠራሮችን፣ ልግመኝነትን እና በተለይም የተደራጀ ሌብነትን በጽኑ ይታገላል። የሕግ የበላይነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ የተደራጀ ሌብነትን ከምንጩ ለማድረቅ ይሠራል። የሀገራችን ዜጎች ለፍተው በሥራ እና በጥረታቸው ሀብት የሚያፈሩባት እንድትሆን ፓርቲያችን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ጠንክሮ የሚሠራውን ያህል፣ ሕዝብን እና ሀገርን በሚጎዳ አቋራጭ መንገድ ወይም በሌብነት ሀብት ለማግኘት የሚፈልጉትን ደግሞ በጽናት በመታገል፣ ማኅበረሰባችን የግብረ ገብ ውኃ ልኩን ጠብቆ እንዲጓዝ ይታገላል።

## 2.2.3 ዘላቂና አዎንታዊ ሰላምን ማረጋገጥ

2.2.3.1 ፓርቲያችን ሀገራችን ህልውናዋ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ትቀጥል ዘንድ ሰላሟ ሊጠበቅላት ይገባል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የማኅበራዊ ሀብቶቻችንን በመጠቀም ሕዝብና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማስተባበር የሰላም ባህል በመገንባት፣ የሕግ የበላይነትን በማስከበርና ፍትሕን በማስፈን እንዲሁም ሀገራዊ መግባባትን በማጎልበት ፓርቲያችን ግጭትን ማስቆም፣ ዕምቅ ግጭቶችን ለማምከን እና ዘላቂ አዎንታዊ ሰላምን ለማስፈን ይሰራል።

2.2.3.2 ፓርቲያችን ከኅብረተሰብ ውስጥ የሚጀምር የሰላም እንቅስቃሴ ከየትኛውም መንግሥታዊ ኃይል በላይ ሀገርን በሰላም የመምራት ታላቅ ጉልበት አለው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ እንዲቻል በኅብረተሰቡ ውስጥ የግጭት ቀስቃሽ አስተሳሰቦችና ተግባራትን የሚጠየፍ ሕዝባዊ ባህልን ለማዳበር በተቀናጀ መልኩ ይታገላል።

2.2.3.3 ፓርቲያችን ዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ግብ ከዴሞክራሲ፣ ከመልካም አስተዳደር እና ከልማት ፕሮግራሞቻችን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም አዎንታዊ ሰላምን ለማረጋገጥ የልማት ሥራዎችና ፍትሐዊነት ማረጋገጥ፣ ያልተማከለና አካታች የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ብዝኃነትን ማክበር እንዲሁም የጋራ ሕልምና ራእይ በመፍጠር ለጋራ ዓላማ ስኬት በጋራ መንቀሳቀስ የሚያስችል የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሥራዎችን አቀናጅቶ በመሥራት ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ይሠራል።

2.2.3.4 የሕግ እና የፍትሕ ተቋማት ምንም እንኳን ተፈጥሯዊ ተግባራቸው የሆነውን ሕግና ሥርዓት ለማስፈን የሚያገለግሉ እንጂ ዜጎችን አፍኖ እና ጨቁኖ ለመግዛትና የገዥዎችን ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ እንዳይውል ፓርቲያችን የሕግና የፍትሕ ተቋማት መሠረታዊ ዓላማ እና ተግባር የዜጎችን መሠረታዊ ነጻነት፣ መብት፣ እኩልነት በሚያከብር እና የጋራ ጥቅም፣ የማኅበራዊ ፍትሕ፣ ብልጽግና፣ ሰብአዊ ደኅንነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ሕግና ሥርዓትን ለማስፈን ይታገላል። የሕግ ገዥነት መርሖች ማስከበር የሚያስችል እንዲሁም መንግሥት ማኅበራዊ እና ተቋማዊ የሆነ የሕግ ገዥነት ባህል መፍጠር እንዲችል የሚያግዝ ንቁ የሆነ የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ይታገላል።

2.2.3.5 ዘመናዊና ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በጣምራ በመጠቀም፣ ዕምቅ ግጭትን ማወቅ፤ የቅድመ ዝግጁነትና የምላሽ ዐቅምን በማዳበር ግጭትን ማምከን እና በትምህርትና በሚዲያ የታገዘ የኅብረተሰብ ሰላማዊ ባህል በማዳበር ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ፓርቲያችን ይታገላል።

# ክፍል ሦስት

## III. የኢኮኖሚ ፕሮግራም

### 3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ዓላማ፡- ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት

የብልጽግና ፓርቲ በኢኮኖሚ ፕሮግራሙ የሕዝባችን ሰፊ ክፍል የሆነውን አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ወጣት፣ ሴቶች እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የከተማ ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት በመገንባት የሕዝባችንን የጋራ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ዓላማ ይኖረዋል። ፓርቲያችን በሀገራችን ምርታማነትን እና ፍትሐገዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መንግሥት ወሳኝ አቅምና መሣሪያ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የመንግሥት በኢኮኖሚው ሥርዓት ውስጥ ያለው ተሳትፎ የገበያ መርሕን በመከተል ስትራቴጂካዊ በሆነ ሁኔታ ሀብት የሚፈጥር፣ በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ማሕቀፍ ውስጥ የግሉን ዘርፍና ሌሎች የኢኮኖሚ ተዋናዮችን ተሳትፎ በማጎልበት ምርታማነትን በላቀ ደረጃና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያሳድግ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህም መሠረት ፓርቲያችን ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንዲሁም ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋገጥ አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ጎዳና ለማሸጋገር ያልማል።

### 3.2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች

#### 3.2.1 የብዝኃ ዘርፍ የኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት

3.2.1.1 በአንድ ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የተመሠረተ

የኢኮኖሚ መዋቅር ዘላቂ ዕድገትንም ሆነ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን እንደማያረጋግጥ ፓርቲያችን ያምናል። ስለሆነም ሀገራችን አንፃራዊ ዕምቅ አቅሞችን ታሳቢ

በማድርግ ከግብርና በተጨማሪ የኢንዱስትሪ እና ተዛማጅ የአገልግሎት ዘርፎችን በማሳደግ ኢኮኖሚያችን በብዝኃ ዘርፍ የተዋቀረና ዘላቂ ዕድገት ያለው እንዲሆን ይሠራል። ይህን ለማሳካት ፓርቲያችን ሀገራችን ዕምቅ ጸጋ የታደለችባቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎችን በሙሉ ዐቅም አሟጦ ወደ ልማት የማስገባት የኢኮኖሚ አቅጣጫን ይከተላል።

3.2.1.2 ፓርቲያችን ሀገራችን ለግብርና ዘርፍ ያላትን የሥነ ምኅዳር ተስማሚነት፣ የመሬት እና ሰፊ የሰው ሀብት በሙሉ አቅም ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግና የውሃ ሀብታችንን ማዕከል ያደረገ ልማትን ለማምጣት፣ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የወጭ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ እና የገቢ ምግብ ነክ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት በትጋት ይሠራል። ይህም እንዲሆን ለማድረግ የግብርና ዘርፉ በግብአትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት እንዲሁም አመራረትና የገበያ ትሥሥር መሠረት ያደረገ ግብርናን የማዘመን ስራ ይሠራል። ግብርናን በማዘመን ረገድ የተቀናጀ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ የግብርና አሠራርን (Regenerative Agricul-ture) በማስፋፋት፣ አነስተኛ ይዞታ ላላቸው አርሶ አደሮች በቂና የተሟላ ግብአት እንዲቀርብ በማድረግ፣ የህብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከርና በማስፋፋት፣ የገጠር ፋይናንስ ተደራሽነትን በማስፋት፣ የፋይናንስ ተቋማት ለግብርናው ዘርፍ በቂ ፋይናንስ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ የመስኖ ልማት፣ ሜካናይዜሽን፣ የግብርና ማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት፤ የከተማ ግብርናን በማስፋፋት እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ ምርታማነትን ለመጨመር ይሠራል። ግብርናችን የአየር ንብረት ተጽዕኖን የሚቋቋም እንዲሆን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና የተራቆቱ አካባቢዎች በደን እንዲሸፈኑ ፓርቲያችን ይሠራል።

አርብቶ አደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን በሚኖርባቸው አካባቢዎች ያሉ የተፈጥሮ ጸጋዎች መሠረት በማድረግ

ከህዝቡ የኑሮ ዘዬ ጋር የተጣጣመ የተቀናጀና ዘመናዊ የአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ልማት በተለይም ዘመናዊ የእንስሳት ርባታና ልማት ፕሮግራም በመንደፍ ፓርቲያችን ለአርብቶ አደር ሕዝቦች ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ይታገላል።

3.2.1.3 ኢንዱስትሪ የጠንካራና ዘመናዊ ኢኮኖሚ መሠረት እንደመሆኑ ዘርፉ በሀገራችን ኢኮኖሚ የሚሸፍነው ድርሻ እንዲሰፋ ፓርቲያችን በቁርጠኝነት ይሠራል። የኢንዱስትሪ ልማታችን ዋነኛ መርሕ ኤክስፖርት መር ይሆናል። ሆኖም ግን ፓርቲያችን ሀገራችን የምታስገባቸውን የውጭ ሸቀጦች በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ፖሊሲን የውጭ ንግዳችንን ከማሳደግ ጋር አስተሣሥሮ ይተገብራል። ይህም እንዲሆን ዘርፉ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ጠንካራ የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትሥሥር እንዲኖረው የሚያደርግ፣ ምርታማነት፣ ጥራት፣ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ አቅጣጫን ይከተላል። የኢኮኖሚ ሽግግርን ለማፋጠን የግብርና እና ኢንዱስትሪ ዘርፉን ትሥሥር የሚያጠናክርና ሀገራችንን በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ቀዳሚ ማዕከል እንድትሆን የሚያስችሉ ሥራዎችን በብዛት ይሠራሉ። ስለሆነም ዘርፉን ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ሳቢ፣ ትርፋማና አዳጊ ሊያደርጉ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ ምቹ የኢንቨስትመንትና ንግድ አካባቢን በመፍጠር እና የኢንዱስትሪ ሰላም በማስፈን ጠንካራ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ፓርቲያችን ይሠራል። ፓርቲያችን ግብርናን መሠረት ላደረጉ ኢንዱስትሪዎች፣ ለሰፊ የተማረ የሰው ኃይል ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ እና በስፋት ገቢ ምርቶችን መተካት የሚያስችሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ የሚያደርግ አቅጣጫን ይከተላል።

3.2.1.4 ሀገራችን ያላትን የማዕድን ሀብት በልክ እና ቀጣዩን ትውልድ በማያራቁት መልኩ ለመጠቀም የማዕድን ጥናት፣ ፍለጋ እና ማውጣት እንዲሁም ለገበያ ማቅረብ

ላይ ባለሀብቶች በተለይም የሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶች በተናጠልም ይሁን ከመንግሥት ጋር በመተባበር እንዲሳተፉ ፓርቲያችን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የማዕድን ፍለጋ እና የማውጣት ሥራ ዘመናዊ እና የአካባቢው ማኅበረሰብ ላይ የደኅንነት ሥጋት የማይጥል እንዲሁም ከልማቱ ፍትሐዊ ተጠቃሚነቱንም የሚያረጋግጥ እንዲሆን ፓርቲያችን ይሠራል።

3.2.1.5 የአገልግሎት ዘርፍ በባህሪው በአንድ በኩል በራሱ እንደ ኢኮኖሚ ዘርፍ የሥራ ዕድልና ሀብት የሚፈጥር ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ከፍተኛ የሆነ የአስቻይነት ሚና ይጫወታል። በመሆኑም ፓርቲያችን ሀገራችን ከአገልግሎት ዘርፉ መንትያ የኢኮኖሚ ጥቅም ተጠቃሚ እንድትሆን ይሠራል። በዚህም ረገድ የቱሪዝም ዘርፉን በማልማት እና በማዘመን እንዲሁም የቱሪዝም አማራጮችን በማስፋት ሀገራችን በአፍሪካ ካሉ ዋና ዋና የቱሪስት መዳራሻዎች አንዷ እንድትሆን ፓርቲያችን ጠንክሮ ይሠራል። ይህንንም ለማድረግ የሀገራችንን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ሰው ሠራሽ መስሕቦችን የማስተዋወቅ እንዲሁም ለቱሪስት ፍሰትና ቆይታ ወሳኝ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚያሳድጉ እና ለቱሪስት ምቹ የሚያደርጉ፣ የቱሪዝሙን ዘርፍ የሚያዘምኑ ሥራዎችን ነድፎ ይንቀሳቀሳል።

3.2.1.6 ፓርቲያችን የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ውጤታማነትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሎጅስቲክስ እና መሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት ፈጣን፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና ትስስር እንዲኖር ይሠራል። ሀገራችን የባሕር በር አልባ በመሆኗ የሚያጋጥሙ የወደብ አገልግሎት ችግር ለመፍታት እንዲቻል ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ ወጥ የሆኑ ሥርዓቶች እንዲተገበሩ በማድረግ፣ የባሕር ወደብን በጋራ የማልማት እንዲሁም አገልግሎት የመስጠት ኢንቨስትመንቶች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ፓርቲያችን ይታገላል።

### 3.2.2 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሠረት ያደረገ ማኅበራዊ ፍትሕ ማረጋገጥ

3.2.2.1 የምናስመዘግበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጠቅላላ ሀገራዊ ምርትን ከማሳደግ ባሻገር የሕዝቦችን ሰብአዊ ልማት የሚያመጣ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም ኢኮኖሚያችን ለሁሉም የኢኮኖሚ ተዋንያን ፍትሐዊ እና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተመጣጣኝ የዕድገት ዕድልን የሚፈጥር፣ የዕድገት ምጣኔው እየሰፋና ግለቱን ጠብቆ የሚዘልቅ፣ ጥራቱን የጠበቀና በቀጣይ ትውልድ ኪሣራ ላይ የማይገነባ መሠረተ ጽኑ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ፓርቲያችን ይሠራል።

3.2.2.2 ፓርቲያችን መንግሥት መር ሆኖ የቆየውን ዕድገት ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ሚና አሁን ከሚገኝበት አነስተኛ ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ እንዲል በማድረግ አስፈላጊው ሁሉ ያደርጋል። የምናስመዘግበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት ያለው፣ የአካታችነት እና የዘላቂነት ችግሮችን የሚቀርፍ፣ ምርታማነትን የሚያረጋግጥ እንዲሁም ከከፍተኛ የዕዳ ጫና የተላቀቀ እና ጤናማ የፋይናንስ ሂደትን የተከተለ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን እንዲገነባ ይሠራል። በተጨማሪም አርሶና አርብቶ አደሮችን፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎችን፣ ሴቶችና ወጣቶችን ከኢኮኖሚ ዕድገቱ በተጨባጭ ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ይተገብራል።

3.2.2.3 ልማትን የሚያሳልጥና በየደረጃው ለሕዝቡ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ የሚሆን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መሠረተ ልማት መኖር ለሀገራችን በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ፓርቲያችን በጥብቅ ያምናል። በዚህም መሠረት በመንግሥት፣ በመንግሥትና በግል ባለሀብት ትብብር እና በግል ባለሀብት መዋዕለ ነዋይ፣ ጥራት ያላቸው መሰረተ ልማቶች እንዲገነቡና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ፓርቲያችን በጥብቅ ይሠራል።

3.2.2.4 ፓርቲያችን በፌደራል ሥርዓቱ ማሕቀፍ የበጀት ድልድል፣ የመሠረተ ልማትና የማኅበራዊ ልማት ግንባታና ድልድል እንዲሁም ማንኛውም የሀብት አጠቃቀም የሁሉንም ሕዝቦች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ እንዲፈጸም ይሠራል።

3.2.2.5 ፓርቲያችን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ጋር የተስማሙና የብዝኃ ሕይወት ሚዛንን የጠበቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ያደርጋል። በዚህም በተፈጥሮ ሀብት የታደለችው ሀገራችን በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርጋትን የዝቅተኛ ካርቦን ልቀት እና የታዳሽ ኃይል ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያድግ በማድረግ በሀገራችን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እንዲያብብ ይሠራል።

3.2.2.6 በሁሉም አካባቢዎች ያሉ የልማት ጸጋዎችን በማልማት እንዲሁም በአንፃራዊነት በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የተመጣጠነና ፍትሐዊ ልማት በሁሉም አካባቢዎች እንዲረጋገጥ ፓርቲያችን ይታገላል።

3.2.2.7 ፓርቲያችን በተለያዩ ሀገራትና ዓለም ክፍሎች ከሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ቀውሶች የሚመጡ ጫናዎችን የሚቋቋም የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እንዲሁም የኢኮኖሚ ነጻነት ያለው ሀገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ይሠራል። ይህንንም ለማድረግ ፓርቲያችን ሀገራዊ ፍላጎት እና አቅርቦትን ለማጣጣም ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። ይህም ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚረዳ ሰፊ የገበያ ፍላጎትን መፍጠር ብሎም የኑሮ ውድነትን መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ሆኖ ውጤታማ የማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያ፣ የፖሊሲ ቀረፃ እና ማስፈጸም ላይ የሚያጠነጥን ዐቅም ግንባታ ላይ አተኩሮ ይሠራል።

3.2.2.8 የፋይናንስ ዘርፉ በቆጣቢ እና በኢንቨስተር የኢኮኖሚ አሐዶች መካከል የሚኖርን የገንዘብ መጠን ፍላጎት በማስታረቅ ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ፓርቲያችን በፅኑ ያምናል። ስለዚህም ዘመናዊ አሠራርና ተወዳዳሪነት የሰፈነበት መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የፋይናንስ ዘርፍ እንዲኖር ይታገላል። ይህም ሲሆን በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካታች የሆነ የፋይናንስ አገልግሎት በማስፋፋት እና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት ላይ ትኩረት በማድረግ ይሠራል።

## 3.2.3 ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት

3.2.3.1 ዘላቂ እና አስተማማኝ ብልጽግና የሚረጋገጠው ኢኮኖሚው ዕውቀትን እንደ ግብአትም ሆነ እንደ ምርት የሚጠቀም ሆኖ ሲገነባ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም በቴክኖሎጂ ዕድገት፣ በኢኖቬሽን እና በሰው ኃይል ልማት ላይ ያተኮረ የዕድገትና የልማት አቅጣጫ ከረጅምና መካከለኛ ጊዜ አኳያ መፈጸም ዋነኛ የፓርቲያችን ኢኮኖሚ ግብ አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

3.2.3.2 በሀገራችን ቀጣይነት ላለው ምርታማነት እና የሕዝብ ኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ቁልፍ የሆነው ዕውቀት እና ሳይንሳዊ ምርምር ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ፓርቲያችን ዕውቀትን መሠረት ያደረገ ቴክኖሎጂ፣ የቢዝነስ ፈጠራ እንዲሁም በዘመናዊ የአመራርነት ክሂሎቶች እና በተቋማት ግንባታ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ያደርጋል።

3.2.3.3 ፓርቲያችን ዕውቀት መር ኢኮኖሚ የሚገነባው ለሰው ኃይል ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ነው

ብሎ ያምናል። በመሆኑም ተወዳዳሪ፣ ምርታማና፣ ጤናማ የሰው ኃይል ልማት ላይ ትኩረት ያደርጋል። የኢኮኖሚውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ገበያን መሠረት ያደረገ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረግ ብቁ እና ውጤታማ የሰው ኃይል በማልማት በዕውቀት የሚመራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፓርቲያችን ይሠራል።

## 3.2.4 ከተሜነት እና የከተማ ልማትን ማስፋፋት

3.2.4.1 ፓርቲያችን የገጠር ልማትንና የከተማ ልማትን በማቀናጀትና በማስተሳሰር ዜጎች በያሉበት በሀገራዊ ልማቱ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ እንዲሁም ከግብርና ልማት ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን ከተሜነትን ለማስፋፋት ይታገላል። እንዲሁም የገጠር ማዕከላት፣ የገጠር ልማትንና የከተማ ልማትን በማስተሣሠር ለመዋቅራዊ ሽግግር አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ይሠራል። የከተሞችን ሽፋን ዓለም አቀፋዊ ስታንዳርዱን ጠብቆ የከተማው ነዋሪ ድርሻ ከገጠሩ የሚኖረው ምጥጥን ከፍ እንዲል ይሠራል።

3.2.4.2 ፓርቲያችን ከተሞች ጽዱ፣ ለኑሮ ምቹና አረንጓዴ እንዲሆኑ የተቀናጀ የከተማ ልማትን ፕሮግራም ነድፎ ይሠራል። ከተሞች የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማቶችን አቅርቦት እንዲያገኙ፣ ሞያዊ ብቃትን መሠረት ያደረገ ጠንካራ የከተማ አስተዳደር እና የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖራቸው በማስቻል መሠረታዊ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ ጥራት ያላቸው እና የሕዝብን ፍላጎት የሚያረኩ እንዲሆኑ ፓርቲያችን ይሠራል።

3.2.4.3 ዘመናዊና የከተሞችን የዕድገት ሁኔታ ያገናዘበ የመሬት ልማትና አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት

በመዘርጋት የከተማ መሬት አቅርቦትንና አጠቃቀም ግልጽ፣ ልማትን የሚደግፍ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ይደርጋል።

3.2.4.4 ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፤ በግል ዘርፍ ሰፊ ተሳትፎ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎችን ማጠናከርና የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማቶችን ያቀርባል።

3.2.4.5 ፓርቲያችን ከተሞችን ከከተሞች እንዲሁም ክልሎችን ከክልሎች በሚያዋስኑ ስፍራዎች በጥናት ላይ የተመሠረቱ የኢኮኖሚ ትሥሥርንና የልማት ኮሪደሮችን በማልማት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ይታገላል::

3.2.4.6 ለኢኮኖሚው ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትንና ሕግጋትን እንዲሁም የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መንገድ ዘርፉ በገበያው ተወዳዳሪ እንዲሆን እንዲሁም ሀገር በቀል ኩባንያዎች የሚጠናከሩበትን አሠራር በመተግበር ወደ ውጤታማነት እንዲሸጋገር ይሠራል።

3.2.4.7 ፓርቲያችን የዜጎች መሠረታዊ ፍላጎት የሆነውን የመጠለያ ጥያቄ ለማሟላት በተለይም በከተሞች ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ቤት የሚያገኙበት አሠራር፣ የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦቶችን ይዘረጋል። በከተሞች የመኖሪያ ቤት ልማት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት፣ ወጪ ቆጣቢና ስፋት ያለው የቤት አቅርቦት በከተሞች እንዲኖርና የመሬት ፍጆታን በቀነሰና የወለል ከፍታን በሚጨምር መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የቤት አቅርቦት ችግርን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ይሠራል።

# ክፍል አራት

## IV. ማኅበራዊ ፕሮግራም

### 4.1 የየማኅበራዊ ፕሮግራም ዓላማ፡- ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማኅበራዊ ልማት

ሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት መነሻዋ ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ ሁለንተናዊ ማኅበራዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ጉዳይ የፓርቲያችን የማኅበራዊ ፕሮግራም አንድ ዋና ትኩረት ይሆናል። በመሆኑም የማኅበራዊ ልማት ሥራዎቻችን የዕድገትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት መንትያ ግቦችን የማሳካት ጉዳይ ይሆናል። ማኅበራዊ የልማት ሥራዎቻችን ከችሮታና ከነባሩ የማኅበራዊ ደኅንነት ትኩረት ወጥቶ ችግሩን ከመብት አንፃር የሚመለከተው ይሆናል። የማኅበራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ተደራሽነትና አካታችነት ባለው መልኩ የማኅበረሰብን ጤና፣ ደኅንነት እና ምቾት የሚያስጠብቅ መሆን ይኖርበታል። ማኅበራዊ ፕሮግራማችን ዜጎችን የሚያስተሣሥር፣ ከችግርና ከመከራ የሚታደጋቸው፣ የሀገርን አለኝታነት የሚያሠርጽ እና በሀገራችን አዎንታዊ ሰላምን የሚያረጋግጥ ይሆናል። ማኅበራዊ የልማት ፕሮግራማችን ኅብረ ብሔራዊ ማንነትን መሠረት ያደረገ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብት እንዲሆን ዒላማ አድርጎ መንቀሳቀስ የፓርቲያችን የማኅበራዊ ፕሮግራም ዓላማ መገለጫ ይሆናል። ይህንንም እውን ለማድረግ በማኅበራዊ ልማት ዘርፍ የአርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን፣ እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የከተማ ነዋሪ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት እንዲስፋፋ ፓርቲያችን ይሰራል።

### 4.2 የማኅበራዊ ፕሮግራም ግቦች

#### 4.2.1 ፍትሐዊነት፣ ጥራት እና አግባብነት ያለው የትምህርትና ስልጠና ስርዓት ማረጋገጥ

4.2.1.1 በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ጨምሮ የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማስፋት እንዲሁም መሃይምነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ ፓርቲያችን ይታገላል፡፡ በዚህም መረት የቅድመ መደበኛና መደበኛ ትምህርት በሀገራችን ሙሉ ለሙሉ እንዲዳረስ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ቢሆንም፤ ትኩረት ሳይሰጠው የቀረውን የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማሳደግ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፡፡

4.2.1.2 ፓርቲያችን በዋናነት የትምህርት ተደራሽነትን አስጠብቆ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የትምህርት ጥራትን ማሳደግ የትምህርት ፕሮግራሙ ዋነኛ ዓላማ አድርጎ ይታገላል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የትምህርት ተቋማት በቁሳቁስና በቴክኖሎጂ የተደራጁ እንዲሆኑ እንዲሁም መምህራን በተሻለ ችሎታና ሥነ ምግባር የታነፁ ሆነው ትውልድን በእውቀት እና በሥነ ምግባር ቀራጮች እንዲሆኑ፤ እንዲሁም የሚገባቸውን ክብርና ጥቅም እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይሠራል፡፡

4.2.1.3 የሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ከኢንዱስትሪው የሰው ኃይልና የምርምር ፍላጎት ጋር ያለውን ትሥሥርና አግባብነት ያለው እንዲሆን ፓርቲያችን ይሠራል። የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ ሥርዓቱ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝግጁነት ግምት ውስጥ በማስገባት የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ፍላጎትና ዐቅምን ባገናዘበ መልኩ እንዲቀረጽ ያደርጋል። በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዕውቀትና የጥበብ መናኸሪያዎች፣ ብዝኃነትን የሚያጎለብቱና እርስ በእርስ መቀራረብን የሚፈጥሩ ዓለም አቀፋዊ ዕሴቶችና አስተሳሰቦች ማዕከላት እንዲሆኑ ፓርቲያችን አበክሮ ይሠራል።

4.2.1.4 የቴክኒክና ሞያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ ዐቅማቸው እንዲጎለብት ተደርጎ ለኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንት የሆነ ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዲያመርቱ ከማድረግ ባሻገር ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሚናው ከፍ ያለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

4.2.1.5 ፓርቲያችን በመጀመሪያ እርከን የትምህርት ቋንቋ ብዝኃ ልሳን እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ብዝኃ ልሳንነቱ የምንገነባውን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከክልሎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

4.2.1.6 የግብረ-ገብ እና ስነ-ዜጋ ትምህርት አብሮነትን በማሳደግና ግብረ ገባዊ ዕሴቶችን በማስፋትና በማስረጽ እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ሀገር ወዳድ ትውልድ በማፍራት ረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ የላቀ እንደሆነ ፓርቲያችን ይረዳል። ስለዚህ የግብረ-ገብና ስነ-ዜጋ ትምህርት እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች አገራዊ አገልግሎት ህብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን የሚያጠናክር፣ የሀገር ፍቅርንና አርበኝነትን የሚያፀና እና ግብረ-ገብነትን የተላበሰ ትውልድ መፍጠሪያ ተደርጎ እንዲቀረጽ ያደርጋል።

4.2.1.7 ፓርቲያችን ሁሉም የትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ነጻነትን ከሚያቀጭጩ እና በዕለት ተዕለት የመማር ማስተማር፣ የምርምር ሥራ ከፖለቲካዊም ሆነ ከአስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነቶች ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ፣ ሁሉም ዕይታዎች በእኩል መድረክ አግኝተው በነጻነት የሚንሸራሸሩባቸው እንዲሆኑ ይሠራል።

## 4.2.2 መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና ሥርዓት መዘርጋት

4.2.2.1 ፓርቲያችን በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ የተመሠረተ የጤና ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል። በተጨማሪም አክሞ የማዳን ዐቅምን በዘላቂነት ለማሳደግ በሰው ኃይል፣ በሥርዓትና በቴክኖሎጂ ዐቅም ግንባታ ላይ ፓርቲያችን ቅድሚያ ይሰጣል።

4.2.2.2 ፓርቲያችን ለእናቶችና ሕፃናት ጤና እንክብካቤ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሠራል፡፡ የሴቶች ጤና የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር ለመቅረፍ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ

እና አጠቃላይ የሴቶችን ጤና ለመጠበቅ ከቅድመ ወሊድ እስከ ድኅረ ወሊድ ድረስ በአቅራቢያቸው በጤና ተቋማት አገልግሎት እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይታገላል። ሀገራችን በጤና ዘርፍ ወደ ኋላ ከቀረችባቸው ዘርፎች አንዱ የሆነው የጨቅላ ሕፃናት ጤና እንክብካቤ ትኩረት እንዲሰጠው ይሠራል።

4.2.2.3 በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ያሉ ዜጎችን ታሳቢ ያደረገ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት አሠራር እንዲዘረጋ ያደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ የጤና መድኅን ሽፋን በመላ ሀገራችን እንዲዳረስ አሠራርን በማዘመን፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደረጃውን የጠበቀ የጤና መድኅን ሽፋን ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረጋል።

4.2.2.4 ፓርቲያችን ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ መሠረት ነው ብሎ ያምናል። ፓርቲያችን የሕዝብ ቁጥሩ ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ጋር ተመጣጥኖ እንዲሄድ፤ እንዲሁም ጤናማ የሆነ ኅብረተሰብ ለመፍጠር የሚያስችል በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራሞች እንዲዘረጉ ያደርጋል።

4.2.2.5 የሕክምና ባለሞያዎች ፍልሰትን በተለይም ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የባለሞያዎችን ፍልሰት ለመቀነስ በገጠር የሚሠሩ ባለሞያዎችን ልዩ ጥቅምን ይሰጣል።

4.2.2.6 የሕክምና ቁሳቁስ እጥረትን ለመቀነስ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። የሕክምና ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚደረግበት ዐቅም እንዲፈጠር ፓርቲያችን ይሠራል።

4.2.2.7 የባህል ሕክምና እንዲዘምን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከዘመናዊ ሕክምና ጋር እንዲደጋገፍና በጥናትና ምርምር እንዲልቅ ያደረጋል።

### 4.2.3 የሀገራችንን አቅም ያገናዘበ ማኅበራዊ የጥበቃ ሥርዓት መዘርጋት

4.2.3.1 የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓታችን ሕዝባችንን ከአስከፊ

ችግርና ከጉስቁልና ኑሮ በመጠበቅ ጤናማ ማኅበረሰባዊ መስተጋብር እንዲኖር ትኩረት አድርጎ እንዲሠራ ያደርጋል። ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ዐቅም ያገናዘበ፣ አካታችና ጥራታቸውን የጠበቁ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓቶችን ፓርቲያችን እንዲዘረጋ ይደረጋል።

4.2.3.2 የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ መብት፣ ክብርና ደኅንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በሙሉ ቁርጠኝነት ይሠራል። የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በተሻለ ሁኔታ በመምራት አካል ጉዳተኞች እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሠራል።

4.2.3.3 ፓርቲያችን አሠሪና ሠራተኛ በሥራ ቦታ ጤናማ የማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው፣ የሥራ ቦታዎች ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ እና የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ይሠራል። ሠራተኛው ከኢንዱስትሪው ምርታማነት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆንና በነጻነት ተደራጅቶ የመንቀሳቀስ መብቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲከበርለት እና አሠሪውም ተገቢ ጥበቃ እንዲያገኝ ይደረጋል።

### 4.2.4 የሴቶችንና የወጣቶች የፖለቲካና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት

4.2.4.1 ሴቶችና ወጣቶች በሚደርስባቸው ሁለንተናዊ ጭቆና ምክንያት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፏቸው ተጠቃሚነታቸው አሁንም በሚፈለገው ልክ አለመሆኑን ፓርቲያችን ይረዳል። በመሆኑም የሴቶችና ወጣቶች ፍትሃዊ ማህበራዊና የፖለቲካ ውክልናና ተሳትፎ እንዲሁም ዘላቂ የሥራ ዕድል፤ የብድር አቅርቦት፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚነት እና ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ እንዲያገኙ ፓርቲያችን ይታገላል።

4.2.4.2 ፓርቲያችን አጠቃላይ ኢኮኖሚና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎቻችን ወጣቱን ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ ይሠራል። ወጣቶች በተማሩት የትምህርት ደረጃ፣ ባላቸው ዕውቀት፣ እንዲሁም በጥናት አዋጪ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲሠማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፋፊ የሥራ ዕድል አማራጮችና ዕድሎች እንዲፈጠሩ ፓርቲያችን ይሠራል። የወጣቶችን የስፖርት ማዘውተሪያዎችና የመዝናኛ ሥፍራዎችን በጥራትና በብዛት በማሳደግ፤ ወጣቶች ንቁና ግብረ ገብነትን የተላበሱ እንዲሆኑ እንዲሁም ከሱስና ከጥፋት የራቁ እንዲሆኑ ፓርቲያችን ይሠራል።

4.2.4.3 ፓርቲያችን የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት በሕግ እና በተቋም ታግዞ ዜጎች ለተገቢ አገልግሎት ተገቢ ክፍያ እንዲያገኙ ክትትል እና ድርድር በማድረግ፤ የዜጎች ደኅንነት እና ክብር እንዲጠበቅ ይታገላል።

## 4.2.5 ብዝኃነታችንን ማዕከል ያደረገ የቋንቋ፣ የባህልና ቅርስ ልማት

4.2.5.1 ኅብረ ብሔራዊ ሀገር የመፍጠር ትልምን እውን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎች እንዲያድጉና እንዲጎለብቱ ሕጋዊ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ ሥራዎች ተግባራዊ ያደርጋል። የኢትዮጵያን ብዝኃነትን በሚገልጽ መልኩ፤ ተጨማሪ የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ፓርቲያችን ይታገላል።

4.2.5.2 ፓርቲያችን ኢትዮጵያዊ የጋራ ዕሴቶችና ባህሎች እንዲጎለብቱ፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችን፣ የሚዳሰሱም ሆነ የማይዳሰሱ ባህላዊና ትውፊታዊ ቅርሶቻችን ተገቢው ክብርና ትኩረት ተሰጥቷቸው፣ ከአደጋ ተጠብቀው፤ ለሀገር ግንባታ መሣሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ እና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ በትኩረት ይሠራል። ፓርቲያችን የቀደሙ ቅርሶችን ከመጠበቅ ባሻገር ዘመን

ተሻጋሪ የትውልድ ዐሻራና ቅርስ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ አበክሮ ይሠራል።

4.2.5.3 ፓርቲያችን ስፖርት አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጤናን ከማረጋገጥ በተጨማሪ፤ ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ መቀራረብን የሚያረጋግጥ የብልጽግና አንድ አካል እንደሆነ ይረዳል፡፡ “ስፖርት ለሁሉም” በሚል መርሕ ሀገራዊ አንድነትንና የሕዝቦችን ወንድማማችነትና እኅትማማችነት ለማጠናከር ስፖርት ተቋማዊና ሕዝባዊ እንዲሆን ይሠራል።

4.2.5.4 ኪነ ጥበብ በዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነቱ ጎልብቶ የሀገራችን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጣናዊ ተጽዕኖ የመፍጠሪያ ኃይል እንዲሆን፤ እንዲሁም ኪነ ጥበብ ለሕዝቦች መተዋወቅ፣ መቀራረብ፣ መግባባትና ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ መቆም ጠቃሚ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም ኪነ ጥበብ የማኅበረሰቡን ጠቃሚ ዕሴቶች ለማጎልበት ተገቢውን ሚና እንዲወጣ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ኪነ ጥበባዊ ሀብት በትምህርትና በሥልጠና እንዲታገዝ፣ የኪነ ጥበብ ተቋማትና ማዕከላት ተስፋፍተው ለሀገር ብልጽግና እንዲውሉ ይታገላል።

# ክፍል አምስት

## V. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም

### 5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና ዓላማ፡- ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት

ፓርቲያችን የውጭ ጉዳይን ከሀገር ውስጥ ጉዳይ የተነጠለ አድርጎ አይመለከትም። ይልቁንም የሀገር ውስጥ ጉዳያችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ለውጦች ነፀብራቅ ሆኖ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ያልዘነጋ ነው። የውጭ ግንኙነታችንም የዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታን የሚያረጋግጥ፤ የሀገር አንድነትን በማስጠበቅ ሀገራዊ ክብርን የሚያጎናጽፍ፤ ሀገራዊ ክብርን በማጎናጸፍ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ይሆናል። ሀገራዊ ክብር የሌለው ሀገር ሀገራዊ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ እንደማይችል ፓርቲያችን በጥብቅ ይገነዘባል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት እንዲሁም የዜጎቿን ክብርና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቀናጀና የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራን እውን ያደርጋል። ሀገራዊ ክብራችንን ለማረጋገጥ እና ጥቅሞቻችንን ለማስከበር፣ አስቀድሞ ግንኙነትን በማደስና በማጠናከር ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን መሥራት ላይ ትኩረት በማድረግ በግንኙነት ብልሽት ምክንያት የምናጣቸውን ሀገራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስከበር አመች ሁኔታ ይፈጥራል። በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን መልካም የሚባል ውጤት ያስመዘገበች ሀገር ብትሆንም የውጭ ግንኙነታችን ከጉድለት እና ከግድፈት የጸዳ አይደለም። ስለዚህ ግድፍቶቹን እና ጉድለቶችን መለየት፣ ማስተካከል እና መሙላት እንዲሁም የነበሩ ጠንካራ ጎኖችን ማስቀጠል የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መሠረቶች ናቸው።

### 5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች

#### 5.2.1 ሀገራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት

5.2.1.1 ፓርቲያችን የዜጎቻችን ክብር የሀገራዊ ክብራችን

ዓይነተኛ መገለጫ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ዜጎቻችን በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሆኑ ክብራቸውን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት ሥራ የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መርሐ ግብር ቁልፍ መርሕ ነው። ፓርቲያችን የዜጎችን ክብር መሠረት ያደረገ ሀገራዊ ክብርን ለማስጠበቅ ዜጎችን መሰረት ያደረገና የዜጎችን መብት በየትኛውም የዓለም ክፍል ሊያስጠብቅ የሚችል የውጭ ግንኙነት ሥራዎችን ይተገብራል።

5.2.1.2 ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍላት ሥራ ፍለጋ ይሰደዳሉ። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ለሥራ የወጡ ዜጎቻችንን ደኅንነት፣ ክብር እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ታሳቢ ያላደረገ የውጭ ግንኙነት የኢትዮጵያን ክብር ሊያስጠብቅ ስለማይችል ፓርቲያችን በውጭ ግንኙነት እነዚህን ዜጎቻችንን ታሳቢ ያደረገ ሥራን ይሠራል። የሀገራችን ዜጎች ከውጭ የሥራ ቅጥር የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና መብቶቻቸውና ክብራቸው የሚጠበቅበት ሁኔታ ከቀጣሪ መንግሥታት ጋር ስምምነትን በመፍጠር እንዲመቻች ያደረጋል።

5.2.1.3 የሀገራችንን መልካም ገጽታና የወደፊት ብሩህ ተስፋ ለውጭው ዓለም የሚያስተዋውቁ የውጭ ግንኙነት ሥራዎች ይሠራሉ።

5.2.1.4 የፓን አፍሪካኒዝም መሠረት የሆነችው ሀገራችን መላው ጥቁር ሕዝቦች የሚያከብሩትና የሚያምኑትን ያህል ፓን አፍሪካኒዝምን የሚያጠናክር የውጭ ግንኙነት ሥራዎችን መተግበር ይኖርባታል። ፓርቲያችን ይህን በመረዳት የፓን አፍሪካኒዝም መሠረትነታችንን የሚያጎሉ ሥራዎች እንዲተገበሩ ያደርጋል።

### 5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት

5.2.2.1 ፓርቲያችን የተሻለው መንገድ በትብብርና ፉክክር መሐል ሚዛን መጠበቅ እንጅ ያልተገባ ፉክክር ተገቢ እንዳልሆነ በማመን የውጭ ግንኙነታችን ፖሊሲና ትግበራ ትብብርን፣ የጋራ ጥቅምን እና ሉዓላዊነትን በማስከበር እና

በማክበር ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ያምናል። ችግሮችን ለመፍታትም ሆነ ሀገራዊ ጥቅምን ለማስከበር ቀዳሚው ነገር ግንኙነትን ማደስ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም በፉክክር እና በመቀናቀን ከሚመጣ አንፃራዊ ጥቅም ይልቅ ከውስጣዊ ፍላጎታችን የሚመነጭ ጥቅምን የሚያስቀድም የውጭ ግንኙነት በመከተል አጋሮቻችን ለማስፋትና ግንኙነትን ለማጠንከር አበክሮ ይሠራል።

5.2.2.2 የምንኖርበት ዓለም ባለ ብዙ ዋልታ እንደመሆኑ ከየትኛውም ዋልታ ዲፕሎማሲያዊ ጥግ ሳንይዝ በዋልታዎች መካከል ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ሀገራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር ይሠራል። ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ከነባር አጋሮች ጋር የነበረ ግንኙነት እንዲጠናከር ከመሥራት ባሻገር ከአዳዲስ አጋሮች ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ይደረጋሉ።

### 5.2.3 የብዙዮሽ ትብብር ተቋማት ተሰሚነትን መጨመር እና ፖሊሲያዊ ነጻነትን ማስከበር

5.2.3.1 የብዙዮሽ ዲፕሎማሲን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ተሰሚነታችንን ማሳደግ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ሉዓላዊነታችንን የጠበቀ መልካም ግንኙነትን መፍጠር ላይ ፓርቲያችን ይሠራል። የፖሊሲ ነጻነታችንንና ሉዓላዊነታችንን ባስጠበቀ መልኩ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የባለ ብዙዮሽ ትብብርን ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች ይሠራል። ፓርቲያችን ሀገራችን በብዙዮሽ ዲፕሎማሲ የአፍሪካ ድምጽ በመሆን የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል እንድትሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

### 5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

5.2.4.1 ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመፍጠር አካባቢያዊ ሰላም እንዲረጋገጥ ፓርቲያችን በትኩረት ይሠራል። የአካባቢያዊ ሰላም ችግር የሆኑ ሽብርተኝነትና ሌሎችም የሰላም ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን ለመግታት ከጎረቤትና ሌሎች

ሰላም ወዳድ ሀገራት ጋር በመሆን በቅንጅት ይሠራል። በተጨማሪም ለአካባቢያዊ ሰላም መደፍረስ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በጎረቤት ሀገራት መካከል ያሉ መልካም ያልሆኑ ግንኙነቶች እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት ውስጥ ያሉ አለመግባባቶች ቀጣናዊ ችግሮችን ከመፍጠራቸው በፊት በሰላማዊ መልኩ መግባባት እንዲፈጠርባቸው የማግባባት ሥራዎች ይሠራል።

5.2.4.2 በቀጣናው ካሉ ሀገሮች ጋር የጋራ ጥቅሞቻችንን መሰረት ያደረገ አካባቢያዊ የልማት፣ የኢኮኖሚ እና የሰላም ትሥሥር እንዲፈጠር በትብብር ይሠራል። ይህም ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ትሥሥር እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል። ይህንንም ለማድረግ በቀጣናችን ያሉ ነባር አካባቢያዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ለማድረግ እንዲሁም ድርጅቶቹ ለቀጣናዊ ትሥሥር መፈጠር መሠረት እንዲጥሉ በትኩረት ይሠራል። በተጨማሪም እነዚህ አካባቢያዊ ድርጅቶች የቀጣናው የተበታተኑ ድምፆች ወደ አንድ መሰባሰቢያ በማድረግ የቀጣናው ሀገራት የመደራደሪያ ዐቅም እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል።

5.2.4.3 ከጎረቤቶቻችን ጋር በሚያገናኙን የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በጋራና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርሕ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ፓርቲው ይሠራል። ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችንን የመጠቀም መብታችንን ባከበረ፣ ዓለም አቀፍ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መርሖችን በተንተራሰ መልኩ ለጥቅም እንዲውሉ ይደረጋል። እንዲሁም በአጠቃቀም ምክንያት የሚመጡ አለመግባባቶችም በዓለም አቀፍ መርሖችና በዲፕሎማሲያዊ መንገዶች እንዲፈቱ በዘላቂነትም በወንዞቹ ላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ ስምምነት እንዲደረስ ያደርጋል። በተመሳሳይ ሀገራችን በአካባቢያችን ካሉ ባለ ወደብ ሀገሮች የተሻለ የወደብ ተጠቃሚነት መብት በሚያረጋግጥ መልኩ አካባቢያዊ ትብብሮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሠራ ያደርጋል።

### 5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ተሳትፎ ማሳደግ

5.2.5.1 ከሀገራቸው ጋር የተለየ ቁርኝት ያላቸው በውጪ የሚኖሩ

ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የማኅበራዊ ሁኔታዎች የተነጠሉ እንዳይሆኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በዚህ ጉዳይ ኤምባሲዎቻችን ከምንም ጊዜ በላይ በውጪ ላሉ ዜጎች እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቅርብ ይሆናሉ። ለመብቶቻቸው ቀድሞ ደራሽና ጠበቃ፣ ለደኅንነታቸው ቀዳሚ ዋስትና እንዲሆኑ ይደረጋል።

5.2.5.2 በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ባለቤት እንዲሆኑ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በየሚኖሩበት ሀገር የኢትዮጵያ አምባሳደሮች እንዲሆኑ በማበረታታት ላይ በትኩረት ይሠራል፡፡

### 5.2.6 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት የመፈጸም ዐቅም መገንባት

5.2.7.1 ፓርቲያችን የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት እንዲሁም የዜጎቿን ክብር እና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ሀገራዊ ክብራችንን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቀናጀ እና የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራ እውን ያደርጋል። የውጭ ግንኙነት ተቋሞቻችን የውጭ ግንኙነትን የማስፈጸም ዐቅማቸው የላቀ እንዲሆን የመምራት ዐቅም ባላቸው አመራሮችና የመፈጸም ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች እንዲዋቀሩ ያደረጋል። አምባሳደሮቻችን የሀገራችንን ስምና ክብር እና የኢትዮጵያን አንድነት የሚያንፀባርቁ መሆን እንዳለባቸው ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም አምባሳደሮች ሀገራችንን እና ታሪኳን ጠንቅቀው የሚያውቁ እና ሀገራዊ ክብራችንን የሚያስጠብቁ፣ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ዕውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል። በተጨማሪም የውጭ ግንኙነት ዘርፉና ተቋማት ወቅቱን ባገናዘበ ሀገራዊ ሁኔታዎች እና ዓለም አቀፍ ዕድገቶች በተቃኘ መልኩ እንዲያድጉ እና እየተለወጡ እንዲመጡ ይሠራል።

5.2.7.2 ፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት ማስፈጸሚያ ሀገራዊ ዐቅማችን በሀገር ኃይል አቅማችን ላይ እንዲመሠረት ሰፊ ጥረት ያደርጋል። ይህም ካለን ወረት በተጨማሪ በቀጣይ በሚከናወኑ የመልካም ገጽታና አዎንታዊ ተጽዕኖ

የመፍጠሪያ ተግባራት በመነሣት እየተገነባ የሚሄድና በጎረቤቶቻችንም ሆነ ከሌሎች ሀገራት ጋር በምንፈጥረው መተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል። ለዚህም በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

5.2.7.3 የሀገራዊ ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጉዳይ በሀገር ኃይሎች ዐቅም ብቻ የሚመለስ ባለመሆኑ ሀገራዊ ክብራችን ሳይደፈር የመግታት ዐቅም ያለው ጠንካራ፣ ዘመናዊና ሁሉን አቀፍ ወታደራዊ ኃይል መገንባት ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም የመከላከያ ዐቅማችን የዘመኑን ዐውደ ውጊያ የዋጀ፣ በዋናነት ጥቃትን ከወዲሁ የማስቀረት ዐቅምን መሠረት የሚያደርግ፣ በማንኛውም መስክ የሚቃጡትን ትንኮሳዎች መመከት የሚችል፣ ለዜጎቻችን ኩራት በሚሆንና ሀገራዊ ጥቅማችንን በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲደራጅ ይሠራል።

5.2.7.4 ፓርቲያችን ሀገራዊ ክብራችንን እና ሀገራዊ ጥቅማችንን ሊያስከብር የሚችል ዘርፈ ብዙ ዲፕሎማሲን የመተግበር ዐቅማችንን ማሳደግ እና ከመተግበር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሁሉን አቀፍ ዲፕሎማሲን በመተግበር የትብብር ዘርፎችን ማስፋት ፓርቲያችን ቅድሚያ ሰጥቶ ይሠራል። በዚህም የሰላም፣ የኢኮኖሚ፣ የዜጋ ተኮር እና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ መተግበሪያ ስትራቴጂ ሆነው እንዲሠራባቸው ትኩረት ይሰጣል። በሌላ በኩልም ለመገንባት ለምንጥረው ዕውቀት መር ኢኮኖሚ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከሚፈለገው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ ብሎም ከቀደሙት ሀገራት ልምድን ለመቅሰምና የዕውቀት ሽግግር ለማድረግ የሳይንስ ዲፕሎማሲን የሚያጠናክሩ ሥራዎች ይሠራሉ።

**መጋቢት 2014 ዓ.ም**

**ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና)**

**አዲስ አበባ**